# የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን

## የምርት ግብይት የገለልተኛ አዲተር አሠራር መርሆዎችን ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 584/2013 /እንደተሻሻለው/

# በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን

## የምርት ግብይት

## የገለልተኛ ኦዲተር አሰራር

## መመሪያ /እንደተሻሻለው/

በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን

የምርት ግብይት

የገለልተኛ ኦዲተር አሠራር መመሪያ /እንደተሻሻለው/

## መግቢያ

የምርት ገበያው አሠራር አስተማማኝ ግልፅና የተረጋጋ እንዲሆን ለማስቻል፤

የግብይቶችን የፋይናንስ አቋም ለማጠበቅና የገበያ ሥርዓቱን የሚያናጉ አደጋዎች እንዳይከሰቱ ለማድረግ፤

የምርት ገበያውን የአሰራር ደህንነት ለማጠበቅ፣ የደንበኞችን ደህንነት እና በአጠቃላይ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፤

በምርት ገበያ ለማስማራት የሚፈልጉ ባለህብቶች በግብይት ስርአቱ ላይ አመኔታ እንዲኖራቸው ማድረግ እንዲቻል፤

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 551/1999 አንቀጽ 6/8/ እና አንቀጽ 34/2/ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን የምርት ግብይት የገለልተኛ ኦዲተር አሠራር መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### አንቀጽ አንድ

### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን የምርት ግብይት የገለልተኛ ኦዲተር አሠራር ሚሆዎችን ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 584/2013/እንደተሻሻለው/" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ ሁለት

### ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያወስጥ፡-

1. **"ገለልተኛ ኦዲተር"**ማለት በዚህ ክፍል አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገወን አሟልቶ በባለስልጣኑ የገለልተኛ ኦዲተሮች ዝርዝር ወስጥ የተካተተ ድርጅት ወይም ግለሰብ ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የኅብረት ሥራ ማህበራትን፣ የዩኒየኖችን እና የፌደሬሽኖችን ሂሳብ ኦዲት የሚያደርግ አግባብ ያለው የፌደራል ወይም የክልል የህብረት ሥራ ማነበራት ኤጀንሲ ኦዲተርን ይጨምራል፡፡
2. **"ኦዲት ተደራጊ አካላት"**ማለት የምርት ገበያው አባላት፣ የግብይት ፈጻሚዎች ማህበር ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ተቋማት ናቸው፡፡
3. **"የምርት ገበያው አባላት"** ማለት በባለስልጣኑ መመሪያና በምርት ገበያው ደንብ ላይ የተጠቀሱት ተገበያይ አባላት፣ አገናኝ አባላት፣ ወስን ተገበያይ አባላትና ወስን አገናኝ አባላት ናቸው፡፡
4. **"ባለስልጣን"**ማለት በአዋጅ ቁጥር 551/1999 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ነው፡፡
5. **"የምርት ገበያ"**ማለት በአዋጅ ቁጥር 550/1999 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ነው፡፡
6. **"አዋጅ"** ማለት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999 ነው፡፡
7. **"መመሪያ"** ማለት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን መመሪያ ቁጥር 1/2001 /እንደተሻሻለው/ነው፡፡
8. **"ደንብ"**ማለት የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንብ ነው፡፡
9. **"ዝምድና"** ማለት በህግ የታወቀ የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ሆኖ በዚሁ ዝምድና ምክንያት ገለልተኛ ኦዲተሩ ሙያዊ ተግባሩን በአግባቡ እንዳያከናወን ተፅዕኖ ሊያሳድር ወይም ሊፈጥር የሚችል ወይም ይፈጥራል ተብሎ የሚገመት ግንኙነት ማለት ነው፡፡

### አንቀጽ ሶስት

### የመመሪያው አላማ

1. ኦዲት ተደራጊ አካላት የሚያቀርቧቸው የሂሳብ መግለጫዎች እና የህጎች ማክበርን የሚገልጹ ሪፖርቶች ተአሚኒና ትክክለኛ መሆናቸውን ለሚረጋገጥ እንዲቻል፤
2. የምርት ግብይት ስርአቱን አስተማማኝ ግልፅና የተረጋጋ ለማድረግ፤ እና
3. የገበያውን ልዩ ባህርይ በሚዳት በሂሳብ ባለሙያዎች የተሠሩ ሂሳቦች የምርት ገበያውን ልዩ ባህርይ የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን ለሚረጋገጥ እንዲያስችል ነው፡፡

**አንቀጽ አራት**

**የተፈፃሚነት ወሰን**

1. ይህ መመሪያ በኦዲት ተደራጊ አካላት የሚቀርቡ የሂሳብ መግለጫዎችን ትክክለኛነት እና የህጎችና ደንቦች ማክበርን ለሚረጋገጥ በገለልተኛ ኦዲተር በሚከናወኑ ኦዲቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም የዚህ መመሪያ አንቀፅ 5፣ አንቀፅ 11 እና አንቀፅ 22 ንዑስ አንቀፅ /2/ /ሐ/ በህብረት ሥራ ማህበራት ኤጀንሲ ኦዲተሮች ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም፡

**አንቀጽ አምስት**

**የገለልተኛ ኦዲተር ዝርዝር ስለመያዝ**

1. ባለስልጣኑ የገለልተኛ ኦዲተር ዝርዝር ይይዛል፡፡
2. በባለስልጣኑ የገለልተኛ ኦዲተር ዝርዝር ውስጥ ለመመዝገብ፡ –
   ሀ/ ከፌደራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት የሙያ ፈቃድ ያገኘ፤
   ለ/ በአገሪቱ ህግ መሰረት የኦዲት ስራ ለመስራት በህግ የተቋቋመ ወይም በአገሪቱ የንግድ ህግ መሰረት በንግድ ድርጅትነት የተመዘገበ፣ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ያለው፣ የዘመኑን የንግድ ግብር የከፈለ እና ወቅታዊ የንግድ ፈቃድ ያለው፤
   ሐ/ የምርት ገበያ አሰራርን በተመለከተ ስልጠና ከምርት ገበያ ባለስልጣን የወሰደ፤
   መ/ በደረጃ ሀ እና ለ የተመደቡ ግብር ከፋዮችን የሂሳብ አያያዝ ወይም ተመሳሳይ ተቋማትን ኦዲት ስለማድረጉ መረጃ ማቅረብ የሚችል፤
   ሠ/ አጠቃላይ የኦዲት ድርጅቱን ገጽታ ማለትም የፋይናንስ፣ የሰው ኃይል እና ድርጅታዊ አቋም የሚያሳይ ዝርዝር ማቅረብ የሚችል፤
   ረ/ ከፌደራል ዋና ኦዲተር የሙያ ፈቃድ ካገኘ በኋላ ባለፉት የሚጨርሻዎቹ ሁለት ተከታታይ ዓመታት ያከናወናቸውን የኦዲት ሥራዎችና ከኦዲት ወጪ አገልግሎት የሰጣቸውን ግለሰቦችና ድርጅቶች የሚገልፅ ዝርዝር ማቅረብ የሚችል፤
   ሰ/ ከዚህ ቀደም በኢኮኖሚ ገንዘብ ነክ ወይም የገለልተኛ ኦዲተሩን ስብዕና በሚቀንሱ ወንጀሎች ጥፋተኛ ያለመሆኑን የሚገልጽ መረጃ ማቅረብ የሚችል፤
   ሸ/ እንደአስፈላጊነቱ በባለስልጣኑ የሚጠየቁ ሌሎች መረጃዎችን ማቅረብ የሚችል፤ መሆን አለበት፡፡

3. ከአንድ በላይ የሆኑ በግል የሚሠሩ ኦዲተሮች በአንድ ላይ ሆነው የንግድ ማኅበር ሲያቋቁሙ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የኦዲት ድርጅቶች ሲዋሀዱ በቅደም ተከተላቸው መሠረት ቢያንስ አንዱ ኦዲተር ወይም አንዱ የኦዲት ድርጅት በንግድ ማህበሩ ወይም በውህደቱ ከመቃቀፉ በፊት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር

የተጣለከቱትን መሥፈርቶች የሚያሟላ መሆኑ ሰረጋገጥ ባለሥልጣኑ የተመሠረተወን አዲስ ድርጅት በገለልተኛ ኦዲተሮች ዝርዝር ወስጥ ሊያስገባው ይችላል፡፡

4. ባለስልጣኑ በየጊዜው በገለልተኛ ኦዲተር ዝርዝር የሚዘገባቸውን ገለልተኛ ኦዲተሮች በበጀት አመቱ መጀመሪያ ላይ ለኦዲት ተደራጊ አካላት እና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡
5. በባለሥልጣኑ የገለልተኛ ኦዲተር ለመመዝገብ በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ 2 ከ"ሀ" እስከ "ሸ" የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያረጋግጡ መረጃዎች ከማመልከቻ ጋር መቅረብ አለባቸው፡፡
6. ባለሥልጣኑ የምዝገባ ጥያቄወን ሞሞ መስፈርቱን ለሚያሟላ ገለልተኛ ኦዲተር ስለ መመዝገቡ የሚገልጽ መረጃ በሰባት ቀን ወስጥ ይሰጣል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የገለልተኛ ኦዲተር መርሆዎች
### አንቀጽ ስድስት
### አጠቃላይ መርሆዎች

1. ማንኛወም ገለልተኛ ኦዲተር በኦዲት ሞያ ተቀባይነት ያገኙ የስነ ምግባር መርሆዎች እንደተጠበቁ ሆነው የኦዲት ተደራጊ አካላትን ሂሳብ እና የአሰራር ህጋዊነት የሚያረጋግጡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የገለልተኛ ኦዲት መርሆዎች ማክበርና በሞያ ነጻነት ላይ ከሚከሰቱ ስጋቶች ራሱን ማጠበቅ ይገባዋል፡፡
2. ገለልተኛ ኦዲተሩ የሞያ ተግባሩን በሚያከናወንበት ጊዜ ሞያዊ ወሳኔወን ከሚዛቡ ወይም ከሚጓደሉ የኢኮኖሚ የገንዘብ እና ሌሎች ማናቸወም ግንኙነቶች በመራቅ የሞያ ነጻነቱን ማጠበቅ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ 1 የተደነገገው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በገለልተኛ ኦዲተሩ የሞያ ነጻነት ላይ ስጋት ከሚፈጥሩ፡-
    ሀ. የራስን ጥቅም መሻት፤
    ለ. የራስን ስራ መከለስ ወይም መልሶ መስራት፤
    ሐ. ለደንበኛ ጥቅም መቆም፤
    መ. ከደንበኛ ጋር የጠበቀ ግንኙነትና ትወወቅ፤ እና
    ሠ. ሌሎች መሰል የሞያ ነጻነትን ሊያጓደሉ ከሚችሉ ተግባራት መራቅ አለበት፡፡
4. ማንኛወም ገለልተኛ ኦዲተርሞያዊ ተግባሩን በሚያከናወንበትጊዜተአሚኒቱን፣ ሚዛናዊነቱንና ገለልተኝነቱን ሊያጓደሉ ከሚችሉ የጥቅም ግጭቶች መራቅ አለበት፡፡
5. በዚህ ክፍል የተዘረዘሩት የገለልተኛ ኦዲተር መርሆዎች የገለልተኛ ኦዲተሩን የስነ ምግባር ጉድለቶች በሚሸፍኑበት ጊዜ በፌደራል ዋና ኦዲተር የወጡየስነ ምግባር መርሆዎች በማሟያነት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

### አንቀጽ ሰባት
### የራስን ጥቅም መሻት

ማንኛወም ገለልተኛ ኦዲተር በማናቸወም ምክንያት፡-

ሀ/ ከኦዲት ተደራጊ አካላት ወይም የስራ አመራር ሰራተኞች ቀጥተኛ የሆነ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ህገ ወጥ ጥቅም መቀበል፤

ለ/ ለኦዲት ተደራጊው ወይም ለኦዲት ተደራጊው ተቀጣሪ ለሆኑ የብድርም ሆነ የዋስትና አገልግሎት ማስጠት ወይም ከእነሱ መቀበል፤

ሐ/ ከኦዲት ተቋሙ አጠቃላይ ገቢ ወስጥ ከኦዲት ተደራጊው አካል የሚገኘው ገቢ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዝ በመሆኑ ምክንያት ከሚጠበ ያለፈ ጥገኝነት መፍጠር፤

መ/ ከኦዲት ተደራጊ አካላት ጋር የንግድ ግንኙነት መፍጠር፤

ሠ/ ከኦዲት ተደራጊ አካላት ጋር ለኦዲት ቡድኑ አባላት የስራ እድል መፍጠር፤ ወይም

ረ/ የገለልተኛ ኦዲተሩን ሪፖርት በሚጠቀሙ አካላት ዘንድ የገለልተኛ ኦዲተሩን ሙያዊ አስተያየት ሊያዛቡ ወይም ሊቀንሱ የሚችሉ ሌሎች ሁኔታዎች መፍጠር፤ የለበትም፡፡

## አንቀጽ ስምንት
## የራስን ስራ መከለስ ወይም መልሶ መስራት

ማንኛውም ገለልተኛ ኦዲተር ወይም የኦዲት ቡድኑ አባል፡-

ሀ/ የኦዲት ተደራጊ አካል ዳይሬክተር ወይም የስራ ሜ የነበረ ከሆነ፤

ለ/ የኦዲት ተደራጊ ሰራተኛ ሆኖ በሰራተኛነቱ በኦዲት አገልግሎቱ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር የሚችል ከሆነ፤

ሐ/ ለኦዲት ተደራጊ አካል ከኦዲት ውጭ ማንኛውም ሌላ አገልግሎት የሰጠ ከሆነ፤ ወይም

መ/ ሌሎች የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ ሁኔታዎች ወስጥ ተሳትፎ ከሆነ፤ በማናቸውም ምክንያት የኦዲት ተደራጊ አካላትን ሂሳብ ወይም የአሰራር ህጋዊነት ሚረጋገጥ አይችልም፡፡

## አንቀጽ ዘጠኝ
## ለደንበኛ ጥቅም መቆም

ማንኛውም ገለልተኛ ኦዲተር ወይም የኦዲት ቡድኑ አባል፡-

ሀ/ በኦዲት ተደራጊ አካላት አክሲዮኖች ወይም ሌሎች የዋስትና ዶክመንቶች /ሴኩዩሪቲስ/ በምርት ግብይት ወሎች ላይ የተሳተፈ ወይም ሌሎች እንዲሳተፉ ያስተዋወቀ፤

ለ/ ኦዲት ተደራጊ አካላትን በመወከል ከሌላ ከሶስተኛ አካላት ጋር ማንኛውም ስምምነት ወይም ድርድር ያደረገ፤ ወይም

ሐ/ በሌሎች ተመሳሳይ ሁኔታዎች ወስጥ የኦዲት ተደራጊ አካላትን ጥቅም በመወከል የተሳተፈ፤ በማናቸውም ምክንያት የኦዲት ተደራጊ አካላትን ሂሳብ ወይም የአሰራር ህጋዊነት ሚረጋገጥ አይችልም፡፡

## አንቀጽ አስር
## ከኦዲት ተደራጊ አካላትጋር
## የጠበቀ ንግኙነትና ትውውቅ

ማንኛውም ገለልተኛ ኦዲተር ወይም የኦዲት ቡድኑ አባል፡-

ሀ/ ዘመድ በኦዲት ተደራጊ አካላት ድርጅት ወስጥ በሽርክና በኃላፊነት ወይም በስራ ሜነት የሚሰራ ከሆነ፤

ለ/ ዘመድ በኦዲት ተደራጊ አካላት ድርጅት ወስጥ ሰራተኛ ሲሆንና ያለው የስራ መደብ በኦዲት ስራው ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ ሊያሳድር የሚችል ከሆነ፤

ሐ/ ከኦዲት ተደራጊ አካላት የበላይ ሀላፊዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለው ከሆነ፤ ወይም

መ/ ከኦዲት ተደራጊ አካላት ጋር ሌሎች ተመሳሳይ የጥቅም ግንኙነትና ትወዉቅ ያለው ከሆነ፤ በማቸወም ምክንያት የኦዲት ተደራጊ አካላትን ሂሳብ ወይም የአሰራር ህጋዊነት ሚረጋገጥ አይችልም፡፡

## አንቀጽ አስራ አንድ
## ስለ ገለልተኛ ኦዲተር አሜራረጥ፣አመዳደብና
## ስለሚሳበት ሁኔታ

1. ማንኛውም ኦዲት ተደራጊ አካል፡-

ሀ/ ገለልተኛ ኦዲተር መምረጥ የሚችለው ባለሥልጣኑ መዝግቦ ከያዛቸው ገለልተኛ ኦዲተሮች ብቻ ነው፡፡

ለ/ የሚጠወን ገለልተኛ ኦዲተር እና ከኦዲት ተደራጊው ጋር የገባወን ስምምነት የኦዲት ሥራው ከመጀመሩ በፊት ለባለስልጣኑ ማዛወቅ አለበት፡፡

ሐ/ ኦዲት ተደራጊው ከሚጠው ገለልተኛ ኦዲተር ጋር የገባወን ስምምነት ለማቋረጥ የሚየበቃ አለመግባባት ሲኖር ወሉን ከማቋረጡ በፊት ሁለቱም ተዋዋዮች ምክንያታቸውን በማዘርዘር ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለባቸው፡

2. ማንኛውም ገለልተኛ ኦዲተር በተከታታይ ከሶስት ዓመታት በላይ አንድን ኦዲት ተደራጊ አካል ኦዲት ሊያደርግ አይችልም፡ ሆኖም ከአንድ የሂሳብ ዓመት ቆይታ በኋላ ኦዲት ተደራጊወን ኦዲት ሚድረግ ይችላል፡፡

3. ማንኛውም ገለልተኛ ኦዲተር በእያንዳንዱ የኦዲት ሥራ በገለልተኛ ኦዲተሩና በሚየሰማራቸው ባለሙያዎች የተፈረመ የገለልተኝነት ሚረጋገጫ /Confirmation of independence/ ማቅረብ አለበት፡፡ ባለስልጣኑ ለዚህ አፈፃፀም የሚረዳ የገለልተኝነት ሚረጋገጫ ቅጽ ያዘጋጃል፡፡

## አንቀጽ አስራሁለት
## ሥልጠና ስለመስጠት

ባለሥልጣኑ ማንኛውም ገለልተኛ ኦዲተር በምርት ግብይት ላይ ያለወን እወቀት ለማሳልበት እንዲችል በምርት ግብይት አሠራር እና በሌሎች ተመሳሳይ ዘርፎች ላይ በየወቅቱ በባለሥልጣኑ ለተመዘገበ ገለልተኛ ኦዲተር በሚየዘጋጃቸው ስልጠናዎች ላይ መሳተፍ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ሦስት
## የኦዲት ሪፖርት

## አንቀጽ አስራ ሦስት

## የኦዲት ሪፖርት መሰረት

1. ማንኛውም ገለልተኛ ኦዲተር ለባለሥልጣኑ የሚቀርባቸው ማናቸውም የኦዲት ሪፖርቶች ተቀባይነት ባገኙ አለም አቀፍ የኦዲት ስታንዳርድ /International Standards on Auditing//ISA/ መሠረት መከናወን አለባቸው፡፡
2. የኦዲት ሪፖርቱ የኦዲት ተደራጊው የሂሳብ መግለጫዎች ለመካከለኛ እና አነስተኛ ድርጅቶች በወጣው የአለምአቀፍ የሂሳብ መግለጫዎችና ሪፖርት ስታንዳርድ /International Financial Reporting Standard for Medium and Small Sized Enterprises/IFRS for SMEs/ መሰረት መከናወኑን ሊገልጽ ይገባል፡፡
3. የኦዲት ሪፖርቱ ለመካከለኛ እና አነስተኛ ድርጅቶች በወጣው የአለም አቀፍ የሂሳብ መግለጫዎችና ሪፖርት ስታንዳርድ /International Financial Reporting Standard for Medium and Small Sized Enterprises/IFRS for SMES/ መሰረት በተከታታይ አመታት ወጥ በሆነ መልኩ /Consistently/ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው መግለጽ ይኖርበታል፡፡
4. ማንኛውም ገለልተኛ ኦዲተር ለባለሥልጣኑ የሚቀርቡ ማናቸውም የአሰራር ሕጋዊነት /Compliance Review/ የሚያረጋግጡ ሪፖርቶችን በባለሥልጣኑና በምርት ገበያው አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መከናወናቸውን ሚያረጋግጥ አለበት፡፡ ባለሥልጣኑ ለዚህ አፈጻጸም የሚረዳ የሪፖርት ማቅረቢያ ናሙና ያወጣል፡፡

## አንቀጽ አስራ አራት

## የኦዲት ሪፖርት አቀራረብ

1. ማንኛውም ለባለስልጣኑ ከሚቀርብ የኦዲት ሪፖርት ጋር የፋይናንስና የህጎች መከበርን የሚያረጋግጥ /Financial Statement & Compliance Review/፤የግኝት መግለጫ በስራ አመራር ሪፖርት /management letter/ ተካቶ በአባሪነት መቅረብ አለበት፡፡
2. የስራ አመራር ሪፖርቱም –

   ሀ/ በኦዲቱ ወቅት የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶችን፤

   ለ/ በማሻሻያ ሃሳብ ላይ በኦዲቱ ወጤት መሠረት ማስተካከያ ሊደረግባቸው የሚገቡ ሁኔታዎችን፤

   ሐ/ በኦዲቱ ወቅት የተፈጸመ የህግ ጥሰት ካለ፤

   መ/በህግ እንዳይገለጹ የተከለከሉ መረጃዎች ካሉ የመረጃዎቹን አይነትና አለማለጻቸው የሚሰጠውን ጠቀሜታ፣ መያዝ አለበት፡፡
3. ማንኛውም ገለልተኛ ኦዲተር የኦዲት ሪርቱን ለባለስልጣኑ፣ ለምርት ገበያው እና ለኦዲት ተደራጊው ማቅረብ አለበት፡፡

## አንቀጽ አስራ አምስት

## የኦዲት ሪፖርት ይዘት

1. ማንኛውም ገለልተኛ ኦዲተር የሀብትና እዳ መግለጫው ለመካከለኛ እና አነስተኛ ድርጅቶች በወጣው የአለም አቀፍ የሂሳብ መግለጫዎችና ሪፖርት ስታንዳርድ /International Financial Reporting Standard for Medium and Small Sized Enterprises/IFRS for SMES/ መሰረት የተዘጋጀ መሆኑን ሚረጋገጡ እንደተጠበቀ ሆኖ የተጣራ ሃብት /net worth/ በሚያሰላበት ወቅት፡ -

ሀ/ በእጅ የማይዳሰሱ ሃብቶች /Intangible Assets/ በሀብት ስሌት ወስጥ ያልገቡ መሆኑን፤

ለ/ ከጊዜያዊ ሃብት /Current asset/ ወስጥ ለእህት ድርጅት /sister company/ የተሰጠን

ብድር ያላካተተ መሆኑን፤

ሐ/ በምርት ገበያው የአባልነት መቀመጫ ለማግኘት ወይም ለመግዛት የተከፈለወን ወጪ ያላካተተ መሆኑን፤

መ/ በምርትገበያው ለክፍያና ርክክብ ሚፀሚ የተቀመጠወን የዋስትና ፈንድ ያላካተተ ሚሆኑን፤

ሠ/ በአጠቃላይ ሀብት /Total Asset/ ስሌት ወስጥ የሊዝ ኮንትራት ያልገባ መሆኑን ሚረጋገጥ

አለበት፡ ፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ከተጠቀሰው በተጨማሪ፡ -

ሀ/ በሀብት ስሌት ወስጥ የተካተቱት ተሰብሳቢ ሂሳቦች ጊዜያቸው ያለፈባቸውና ሊሰበሰቡ የሚችሉ መሆን ያለመሆኑን ሚረጋገጥ፤

ለ/ በሀብት ስሌት ወስጥ የተካተቱት በቆጠራ የተገኙ ንብረቶች /Inventories/ በትክክለኛ ዋጋቸወየተመዘገቡና ያልተበላሹ እንዲሁም ጊዜያቸው ያላለፈባቸው መሆናቸወን ሚረጋገጥ፤

ሐ/ በቆጠራ የተገኙ ንብረቶች /Inventories/ ለዋስትና ማገባት መዋል ያለመዋላቸወን ሚረጋገጥና መግለጽ፤

መ/ አንዳንድ ዋና ዋና ቋሚ ንብረቶች በሂሳብ መግለጫ ወስጥ የተካተቱት በርግጥ በአካል ስለመገኘታቸው ሚረጋገጥና መግለጽ፤

ሠ/ በታክስ ህጉ መሠረት የተጨማሪ እሴት ታክስ /VAT/ከቋሚ እቃ ግዢ ዋጋ ወስጥ ተቀንሶ መሠራቱን ሚረጋገጥና መግለጽ፤

ረ/ የኦዲት ተደራጊወን የሂሳብ አያያዝ ስርአት በሚፈተሽ የእርጅና ቅናሽ ታሪፍ ስሌት፣ በቆጠራ የተገኙ ንብረቶች የዋጋ ተመን /Inventory Valuation/ ዘዴ እና የካፒታላይዜሽን ዘዴ ወጥና በየአመቱ በተከታታይነት እየተሠራበት መሆኑንና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በወጣው የአፈጻጸም መመሪያ መሰረት ሆኖ ለመካከለኛ እና አነስተኛ ድርጅቶች ከወጣው የአለምአቀፍ የሂሳብ መግለጫዎችና ሪፖርት ስታንዳርድ /International Financial Reporting Standard for Medium and Small Sized Enterprises/IFRS for SMES/ ጋር ሂሳቡን ለማስታረቅ የሚታየወን ልዩነት /Deferred tax liability/ ወይም /Deferred tax Asset/በሚል ሂሳብ መግለጫ ወስጥ መካተቱን ሚረጋገጥ፤

ሰ/ የኦዲት ተደራጊው የእዳ /ግዴታ/ ሂሳብ /Liabilities Account/ ወስጥ የተካተቱት የአበዳሪዎች ወይም የአቅራቢዎች ሂሳብ ትክክለኛነትን ሚረጋገጥ፤ አለበት፡ ፡

## ክፍል አራት

## የአሰራር ህጋዊነትን ስለሚረጋገጥ

## /Compliance Review/

### አንቀጽ አስራ ስድስት

### የአባላትን የአሰራር ህጋዊነት ስለሚረጋገጥ

1. የአባላትን የአሰራር ህጋዊነት ሚረጋገጥ የሚያስፈልገው የደንበኞችን የፋይናንስ ደህንነት ለማጠበቅና በገበያው ላይ በድንገት ከሚከሰቱ የገበያ አደጋዎች ለመከላከል እንዲያስችል ነው፡፡
2. ማንኛውም ገለልተኛ ኦዲተር አጠቃላይ የኦዲት ተደራጊ አካላትን የአሰራር ህጋዊነት ሚረጋገጡ እንደተጠበቀ ሆኖ በተለይም የአባላትን ፋይናንስ ጤናማነት ለማ ምገም እንዲያስችለው፡ –
   - ሀ/ አባሉ ከምርት ግብይቱ ጋር በተያያዘ ከእያንዳንዱ ደንበኛ ወይም ስለ ደንበኛው የተቀበላቸውን ወይም ለእያንዳንዱ ደንበኛ ወይም ስለ እያንዳንዱ ደንበኛ የከፈላቸውን ገንዘቦች የሚያሳዩ የሂሳብ ማዝገቦች ተለይተው ማያዛቸውን፤
   - ለ/ በአባሉ ስም የተቀበላቸውና የተከፈሉ ገንዘቦችን ለይቶ የሚያሳይ የሂሳብ ማዝገብ መኖሩን፤
   - ሐ/ እያንዳንዱ አባል የራሱ እና የደንበኞቹ ገንዘብ እራሳቸውን በቻሉ የባንክ ሂሳቦች ለያይቶ ማስቀማጡን፤
   - መ/ አባሉ በተወካይነት ወይም በራሱ ለሚያደርጋቸው ግብይቶች ከደንበኛው የባንክ ሂሳብ ክፍያ ያለሚፈጸማን፤
   - ሠ/ ከደንበኛው የባንክ ሂሳብ ወደ አባሉ የባንክ ሂሳብ ገንዘብ የተላለፈው በምርት ገበያው ደንብ መሠረት መሆኑን፤
   - ረ/ አባሉ በግብይት መድረኩ ሥራ ከጀሚበት ጊዜ ጀምሮ የተጣራ ሃብቱ በእጅ የሚያዳሰሰውን ሀብት ቀንሶ በሚኖቸውም ጊዜ በምርት ገበያው ከተወሰነው አነስተኛ የተጣራ ሃብት ማጠን ያነሰ መሆን ያለማሆኑንና ያነሰ ሆኖ ከተገኘ ወዲያውኑ ለምርት ገበያው ማሳወቅ ባለበት መሠረት ማሳወቅ ያለማሳወቁን፤
   - ሰ/ አባሉ ለደንበኛው ወል ከሚፈፀሙ በፊት በምርት ገበያው በተደነገገው መሠረት ከደንበኛው ጋር ስምምነት በጽሁፍ የተፈራረመ መሆኑን፤ ሚረጋገጥ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለ ሂሳብ መግለጫዎችና ኦዲት ሪፖርት

## አንቀጽ አስራ ሰባት
## ስለሂሳብ መግለጫዎች

ማንኛውም ገለልተኛ ኦዲተር የደንበኞችን የፋይናንስ ደህንነት ለሚረጋገጥናባለሀብቶችበገበያው ላይ ያላቸውን አመኔታ ለማዳበር እንዲያስችል በሂሳብ መግለጫዎች በተለይም፡ –

ሀ/ በሀብትና እዳ መግለጫ ወይም በልዩ ሁኔታ በሚዘጋጀው የተጣራ ሃብት መግለጫ ውስጥ የተካተቱት ሃብቶች፣ ግዴታዎች ወይም እዳዎችና የተጣራው ሃብት በሀብትና እዳው መግለጫ ቀን በትክክል ያሉ መሆናቸውን፤

ለ/ በትርፍና ኪሣራ መግለጫ ወስጥ የተካተቱት የገቢና የወጪ ሂሳቦች ኦዲት በሚደረጉበት የሂሳብ ዓመት ወስጥ በትክክል የተከሰቱ ልወጦች መሆናቸውን፤

ሐ/ ኦዲት በሚደረግበት የሂሳብ አመት ወስጥ የተከናወኑ ማንኛውም የሂሳብ ልወጦች በሙሉ በሂሳብ መግለጫዎቹ ወስጥ ሳይጓደሉ መካተታቸውን፤

መ/ በአባሉ የሀብትና እዳ መግለጫ ወይም በልዩ ሁኔታ በሚዘጋጀው የተጣራ ሀብት መግለጫ ወስጥ የተካተቱት ሀብቶች በትክክል የአባሉ ወይም የድርጅቱ መሆናቸውን በግዴታ ወይም በእዳ ወስጥ የተካተቱት ደግሞ በትክክል የአባሉ ወይም የድርጅቱ እዳዎች ወይም ግዴታዎች መሆናቸውን፤

ሠ/ በአባሉ የሀብትና እዳ መግለጫ ወስጥና በትርፍና ኪሳራ መግለጫ ወስጥ የተካተቱ ሃብቶች /Asset/፤ እዳዎች /Liabilities/፤ የተጣራ ሃብቶች /equity/ ገቢና /revenue/ ወጪዎች /expenses/ በተገቢው ዋጋቸው የተቀመጡ መሆናቸውን /Asserting about Valuation or allocation/፤

ረ/ በሂሳብ አመቱ መዝጊያ በአባሉ የተከናወኑ የሂሳብ ልወጦች በተገቢው የሂሳብ አመት ወስጥ መያዛቸውን፤ ሚረጋገጥ አለበት፡፡

## አንቀጽ አስራ ስምንት
## የኦዲት ሪፖርቱ ቅርጽ

ማንኛውም የኦዲት ሪፖርት፡ –

ሀ/ የኦዲት ሪፖርቱ ርእስ "ገለልተኛ" የሚለውን ቃል መያዝ፤

ለ/ የገለልተኛ ኦዲተሩን ቋሚ የሥራ አድራሻ፤

ሐ/ በመግቢያው ምእራፍ ኦዲተሩ ኦዲት ሚደረጉን የሚገልጽ ሃሳብ፣ ኦዲተሩ ኦዲት ያደረጋቸውን የሂሳብ መግለጫዎች አይነትና ጊዜ፣ የሂሳብ መግለጫዎቹን አዘጋጅቶ የማቅረብ ሃላፊነት ሙሉ በሙሉ የኦዲት ተደራጊው መሆኑንና የኦዲተሩ ኃላፊነት በኦዲት ወጤቱ መሠረት በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ አስተያየት መስጠት ብቻ መሆኑን፤

መ/ የኦዲት ወሰንን በሚጠቅሰው ክፍል ኦዲተሩ በኦዲቱ ወቅት ያከናወናቸውን ተግባራትና ያጋጠሙትን ወሰንነት እና የሂሳብ አያያዙ ለመካከለኛ እና አነስተኛ ድርጅቶች በወጣው የአለምአቀፍ የሂሳብ መግለጫዎችና ሪፖርት ስታንዳርድ /International Financial Reporting Standard for Medium and Small Sized Enterprises/IFRS for SMEs/ መሠረት መሆኑን፤

ሠ/ አስተያየትን በሚጠቅሰው ክፍል ኦዲተሩ በኦዲት የደረሰበትን ውጤት፤

ረ/ ኦዲቱን ያከናወነው የኦዲት ድርጅት ስም፤

ሰ/ የኦዲት ሪፖርቱ ቀን ሪፖርቱ ተፈርሞ ወጪ የሆነበት ቀን መሆኑን፤

ሸ/ የኦዲቱን አላማ በሚጠቅሰው ክፍል ኦዲቱ ለምን እንደተከናወነና እንዳስፈለገ፤

ቀ/ ኦዲተሩ ኦዲት ሲያከናውን የተጠቀማትን ስልት፤ መግለጽ አለበት፡፡

**አንቀጽ አስራ ዘጠኝ**

**አባሪዎች**

**ማንኛውም ገለልተኛ ኦዲተር ከኦዲት ሪፖርት ጋር የተሚሚውን የበጀት ዓመት፡ -**

ሀ/ የሀብትና እዳ መግለጫ

ለ/ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ

ሐ/ የተጣራ ሃብት መግለጫ

መ/ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት የሚያሳይ መግለጫ

ሠ/ የአባሉን የሀብት ለወጥ መግለጫ /statement of change in owner's equity/፤

ረ/ የስራ አመራር ሪፖርት /Management Letter/፤ በአባሪነት አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

**አንቀጽ ሀያ**

**የኦዲት ሪፖርት የሚቀርብበት ጊዜ**

1. ማንኛውም በኦዲት ተረጋግጦ የሚቀርብ ሰነድ በገለልተኛ ኦዲተር ተረጋግጦ መቅረብ የሚገባው የኦዲት ተደራጊው የሂሳብ ዓመት ባለቀ በመጀመሪያዎቹ አራት ወራት ውስጥ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ኦዲት ተደራጊው በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ለማቅረብ የማይችልበትን ምክንያት በመግለጽ መደበኛው የሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ ከማለፉ በፊት አቤቱታውን በጽሁፍ ሲያቀርብና በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተቀባይነት ሲያገኝ ጊዜው በልዩ ሁኔታ ከሁለት ወራት ለማይበልጥ ተጨማሪ ጊዜ ሊራዘምለት ይችላል፡፡

**<u>ክፍል ስድስት</u>**

**<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>**

**አንቀጽ ሃያ አንድ**

**ክትትልና ቁጥጥር**

1. ባለስልጣኑ የዚህን መመሪያ ተፈጻሚነት የመከታተልና የመቆጣጠር ሃላፊነት አለበት፡፡
2. ማንኛውም ገለልተኛ ኦዲተር ባለስልጣኑ በየጊዜው የሚጠይቃቸውን መረጃዎች የመስጠት እና የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ ሀያ ሁለት**

**የክትትልና የቁጥጥር ተግባራት**

1. የባለስልጣኑ የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ገለልተኛ ኦዲተሩ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ህግን፣ የስነ ምግባር ደንብንና አጠቃላይ የኦዲት ሙያ የሚጠይቀውን አሰራር ተከትሎ ማስራቱን ያረጋግጣሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

   ሀ/ የገለልተኛ ኦዲተሩን ገለልተኝነት እና አጠቃላይ ስነ ምግባር፤

   ለ/ የኦዲት ውጤቱን ተአማኒነት፤

   ሐ/ የገለልተኛ ኦዲተሩን አመራረጥና በኦዲተርነት የተመደቡ ባለሙያዎች ስለሚያሟጠባትና ስለሚሰብት ሁኔታ፤

   መ/ ገለልተኛ ኦዲተሩ ስራውን ያከናወነበት ስልት፤

   ሠ/ ገለልተኛ ኦዲተሩ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ በአለም አቀፍ የኦዲት ስታንዳርድ /ISA/ መሰረት ስራውን ማከናወኑን፤

   ረ/ ገለልተኛ ኦዲተሩ ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት የተከሰቱ አለመግባባቶችን፣ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን እና አለመግባባቶችን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎችን፤

   ሰ/ ከኦዲት ተደራጊ አካላት ስራ አመራር እና ተቆጣጣሪ ቦርድ ጋር የተደረጉ ግንኙነቶችን፤

   ሸ/ ሌሎች ከገለልተኛ ኦዲተር፣ ከኦዲት ተደራጊ እና ከኦዲት ውጤቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን፤

   ቀ/ ኦዲተሩ ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት በባለስልጣኑና በምርት ገበያው በወጡ አዋጆች፣ መመሪያዎችና ደንቦች መሰረት ማስራቱን፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፡፡

**አንቀጽ ሀያ ሶስት**

**ሚስጥርን ስለመግለጽ**

ባለስልጣኑ በምርመራ ሂደት ወይም በማናቸውም ሁኔታ ስለገለልተኛ ኦዲተሩ አሰራር፣ የስነ ምግባር ጉድለት ወይም የሙያ ጥፋት ወይም ሌሎች ጥፋቶች መከሰታቸውን በሚያውቅበት ጊዜ አግባብ ላላቸው የመንግስት አካላት፣ ማለትም

ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት፣ ገለልተኛ ኦዲተሩ አባል ለሆነበት ማህበር፣ ለምርት ገበያ እና ሌሎች አግባብነት ላላቸው አካላት እንዳስፈላጊነቱ ማሳወቅ ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሃያ አራት

## የኦዲት ተደራጊ አካላት ግዴታና ተጠያቂነት

1. ኦዲት ተደራጊ አካላት ከምርት ገበያ ጋር የተያያዙ ግብይቶችን የሚገልጽ ማናቸውም የሂሳብ ሰነዶች የግብይት ውሎችና ማናቸውም ሰነዶች ለገለልተኛ ኦዲተሩ ለምርመራ ማቅረብ አለባቸው፡
2. ኦዲት ተደራጊዎች ለመካከለኛ እና አነስተኛ ድርጅቶች በወጣው የአለምአቀፍ የሂሳብ መግለጫዎችና ሪፖርት ስታንዳርድ /International Financisl Reporting Standard for Medium and Small Sized Enterprises/IFRS for SMEs/ ማስረት ሂሳባቸውን የመያዝ ግዴታ አለባቸው፡
3. ኦዲት ተደራጊ አካላት ለምርመራ ለሚቀርቧቸው የሂሳብ ሰነዶች፣ የግብይት ውሎችና ሌሎች ማናቸውም ሰነዶች ትክክለኛነት ሃላፊነት አለባቸው፡
4. ኦዲት ተደራጊ አካላት ለሚፈጽሟቸው ጥፋቶች ወይም ላደረሷቸው ጉዳቶች በወንጀልና በፍትሃብሄር ማጠየቃቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ አስፈላጊውን አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ ይችላል፡፡
5. ኦዲት ተደራጊ አካላት በገለልተኛ ኦዲተር የተረጋገጠ የሂሳብ ወይም የአሠራርን ሕጋዊነት የሚገልጹ የኦዲት ሪፖርቶች ለባለስልጣኑ በየአመቱ ማቅረብ አለባቸው፡

## አንቀጽ ሃያ አምስት

## የገለልተኛ ኦዲተር ተጠያቂነት

1. ማንኛውም ገለልተኛ ኦዲተር ሙያው የሚጠይቀውን ጥንቃቄ ባለማድረጉ ወይም በህግ ላይ የሰፈሩ ግዴታዎችን ሳይከተል በመቅረቱ ያረጋገጠው የሂሳብ መግለጫ ወይም የሕጋዊነት ማረጋገጫ ሪፖርት ላይ የሠፈሩ ነገሮች ትክክለኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው ወይም የኦዲት ተደራጊውን የፋይናንስ አቋም የሚገልጹ በመሆናቸው በማናቸውም ወገኖች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ገለልተኛ ኦዲተሩ ተጠያቂ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የሠፈረው መግለጫ ሀሰተኛ በመሆኑ ምክንያት የሚደርሱ ማናቸውም ጉዳቶች በፍትሐብሄር እና በወንጀል የሚያስከትለው ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ በገለልተኛ ኦዲተሩ ላይ አስተዳደራዊ የቅጣት እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡
3. እንዲሁም አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድበት ገለልተኛ ኦዲተሩስለፈፀመጥፋትና ስለተወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ ባለስልጣኑ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ያሳውቃል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ስድስት

**መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከጥር 1 ቀን 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አምባሳደር አዲስአለም ባሌማ /ዶ/ር/**

**የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን**

**ዋና ዳይሬክተር**